መመሪያ ቁጥር 1072/2017

የኤክሳይዝ ምልክቶች አስተዳደር ስርአትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

# DIRECTIVE NO. 1072/2025

## A DIRECTIVE TO PROVIDE FOR THE MANAGEMENT OF EXCISE MARKINGS

ግንቦት 2017 ዓ.ም

**May/ 2025**

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## የኤክሳይዝ ምልክቶች አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1072/2017

የኤክሳይዝ ምልክቶች ትክክለኛው የኤክሳይዝ ቀረጥ እንዲሰበሰብ ለማድረግ፣ ህገወጥ ንግድን ለመከላከል እና የህዝብ ጤና እና የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ ከፍተኛ እገዛ ያላቸው በመሆኑ፣

የኤክሳይዝ ታክስ ህጎች እንዲከበሩ በማድረግ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የኤክሳይዝ ምልክቶችን እና የመለየት እና የመከታተል ስርአትን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (በተሻሻለው) አንቀጽ 29 እና 42 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኤክሳይዝ ምልክቶችን አስተዳደር ስርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1072/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) "የተጠቃለለ ማሸጊያ" ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች መያዣዎች የያዘ ማሸጊያ ነው።
2) "ስልጣን የተሰጠው ሰራተኛ" ማለት በታክሱ ባለስልጣን የበላይ ሃላፊ ወይም በበላይ ሃላፊው ስልጣን በተሰጠው ሰው በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ማናቸውንም ተግባር እንዲያከናውን ስልጣን የተሰጠው ሰራተኛ ነው፤
3) "የተዘጋጀ የአልኮል መጠጥ" ማለት ለመጠጥነት እንዲውል የተዘጋጀ እና ለችርቻሮ ገበያ የሚቀርብ የአልኮል መጠጥ ነው፤

## A DIRECTIVE TO PROVIDE FOR THE MANAGEMENT OF EXCISE MARKINGS No. 1072/2025

WHEREAS, it is believed that the excise Markings will highly contribute to the proper collection of excise tax, prevent illicit trade and protect public health and environment;

WHEREAS, it is believed that by properly implementing excise markings and track and trace system the excise tax laws can be properly enforced and transparency and accountability can be achieved;

NOW THEREFORE, the Ministry of Finance with the power vested in it under Articles 29 and 42(2) of the Excise Tax Proclamation (as amended) No. 1186/2020 has issued this Directive.

### PART ONE
### GENERAL PROVISIONS

### 1. SHORT TITLE

This Directive may be cited as the Excise Markings Management Directive No. 1072/2025.

### 2. DEFINITIONS

In this Directive, unless the context otherwise requires:

1) "Aggregated packaging" means any packaging containing more than one unit packet of excisable products;
2) "Authorized officer" means a person authorized by the head of the Tax Authority or his authorized representative to perform any function under this Directive;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

4) “የመረጃ ተሸካሚ” ማለት በመሳሪያ በመታገዝ ሊነበብ በሚችል መንገድ መረጃ የሚያዝበት ነው።
5) “የመረጃ ማከማቻ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች መከታተል የሚያስችል መረጃ የሚከማችበት በምልክቶች አቅራቢ ሃላፊነት ስር ያለ ማከማቻ ነው።
6) “አከፋፋይ” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አምራቾች ወይም አስመጪዎች በመግዛት ለጅምላ ሻጮች ወይም/እና ቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ሰው ነው።
7) “የኤክሳይዝ ምልክት” ማለት በፊዚካል፤ በዲጂታል ወይም በሌላ የታክሱ ባልስልጣን በሚወስነው መልክ የተዘጋጀ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ምልክት ሲሆን፤ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 29 የተመለከተውን “የኤክሳይዝ ቴምብር ይጨምራል። ጥርጣሬን ለማስወገድ በፊዚካል ቴምብር ላይ የሚለጠፈውን የዲጂታል ምልክትንም ይጨምራል።
8) “አስመጪ“ ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ወደአገር ለማስገባት በታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበ አስመጪ ነው፤
9) “ከመስመር ውጪ ያለ ዝርግ መረጃ” ማለት በልዩ መለያ አውጪ የሚዘጋጅ በመረጃ ማከማቻ ውስጥ ያለውን መረጃ ማየት ሳይቻል፤በነጠላ መያዣ እና በተጠቃለለ መያዣ ላይ በተደረገው ልዩ መለያ ውስጥ ያለውን መረጃ ( የጊዜ ማህተምን ሳይጨምር) ነጣጥሎ ማየት የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ ፋይል ነው።

10) “መሳሪያ” ማለት የማምረት ሂደት አንድ ክፍል ሆኖ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ለማምረት ወይም ለማሸግ አገልግሎት ላይ የሚውል ነው።
11) “የአስተዳደር ስርዓት” ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የአስተዳደር ስርአት ሲሆን፤ የኤክሳይዝ ቴምብርን፣ የመከታተያ እና የመቆጣጠሪያ ስርአትን፤ የምርት ሂሳብ አያያዝ ስርአትን እና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሶፍትዌሮችን እና ሃርድዌሮችን ይጨምራል፤
12) “አምራች” ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
13) “የምልክቶች አቅራቢ” ወይም በአማራጭ “የመለያ አውጪ” ወይም “ኩባንያ” ማለት ልዩ መለያ፤ዲጂታላዊ ምልክት እንዲያዘጋጅ፤

3) "Compounded spirit" means a spirit that is ready for consumption as a beverage and put up for retail;
4) “Data carrier” means a carrier representing data in a form readable with the aid of a device
5) “Data repository” means a repository hosted by the Markings Provider issuer and containing all traceability data relating to excisable products;
6) "Distributor" shall mean a person that buys excisable goods from one or more Importers or Manufacturers and then sells them to Wholesalers and/or Retailers.
7) “Excise Markings” shall mean a digital or physical Markings or any other mark that the Tax Authority may approve for affixation or printing on excisable goods in accordance with this Directive and shall include “Excise Stamps” as described in Art 29 of the Excise Proclamation. This may include, for the avoidance of doubt, a physical stamp on which the digital mark has been printed.
8) "Importer" means a person registered as an importer by the Tax Authority to import excisable goods specified under this Directive;
9) “Offline flat files” means the electronic files established and maintained by the Unique ID issuer that contain data in a plain text format allowing the extraction of information encoded in the unique identifiers (excluding the time stamp) used at the unit packet and aggregated packaging levels without accessing the repositories system;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

እንዲያትም እና በተቀናጀ አኳን እንዲያሰራጭ፤ እንዲተክል፤ እንዲያጣጥም፤ እንዲሞክር፤ድጋፍ እና ጥገና እንዲያደርግ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን እንዲያከናውን በታክሱ ባላስልጣን ሃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው።

14) "መያዣ" ማለት በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ለጅምላ ወይም ለችርቻሮ ሽያጭ በሚቀርቡበት ጊዜ የሚታሸጉበት ፓኬት፤ ጠርሙስ፤ ወይም ተመሳሳይ መያዣ ነው፤

15) "አዋጅ" ማለት የኤክሳይዝ ትስ አታዋጅ ቁጥር 1186/2012 ( እንደተሻሻለ) ነው፤

16) "መዝገብ" ማለት በምልክት አቅራቢ የሚያዝ ለተመዝገቡ አከናዋኞች፤ ለተቋማት፤ ለመሳሪያዎች የተሰራጩ ልዩ መለያዎች፤ከተገቢው መረጃ ጋር ተመዝግበው የሚያዙበት ነው።

17) "የተመዘገበ አከናዋኝ" ወይም" "ተአ" ማለት በአንቀጽ 3 ለተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ምልክት በሚደረግባቸው ምርቶች ላይ የተሰማራ ፈቃድ የተሰጠው አምራች፤ ፈቃድ የተሰጠው አስመጪ፤ ፈቃድ የተሰጠው አከናዋኝ ሲሆን፤ በአንቀጽ 10 በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ንግድ ስራ ላይ የተሰማራን ሰው ይጨምራል።

18) "ቸርቻሪ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን እቃ ለመጨረሻው ተጠቃሚ በቀጥታ የሚሸጥ እና ይህንን እቃ በመደበኛነት ለሌሎች ቸርቻሪዎች የማይሸጥ ሰው ወይም የንግድ ስራ ነው።

19) "የታክስ ባለስልጣን" ማለት እንደአግባብነቱ የታክሱ ባላስልጣን ወይም የጉምሩክ ኮሚሽን ነው፤

20) "የጊዜ ማህተም" ማለት አንድ ድርጊት የተፈጸመበት ቀን እና ሰአት በጸደቀው ቅጽ ላይያለማቀፍ የተቀናጀ የጊዜ አቆጣጠርን መሰረት በማድረግ የሚመዘገብበት ነው።

21) "የተለየ መለያ" ወይም በአማራጭ "ተመ" ማለት ከአንድ የተለየ ኮድ ጋር የተዛመደ በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን እቃ ምርት፤ ክምችት ወይም እንቅስቃሴን መከተታል እና መቆጣጠር የሚያስችል በቁጥር ወይም በሃዝ የሚገለጽ መለያ ነው።

22) " ጅምላ ሻጭ " ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን እቃ ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ አከፋፋዮች፤ አስመጪዎች ወይም አምራቾች በመግዛት ለሌሎች ጅምላ ሻጮች እና/ወይም ቸርቻሪዎች የሚሸጥ ሰው ነው።

10) "Machine" means the equipment used for the manufacture or packaging of excisable products which is integral to the manufacturing process;

11) "Management System" means the Excisable Goods Management System and includes excise Markings, a track and trace system, a production accounting system, and related software and hardware.

12) "Manufacturer" means a manufacturer licensed to manufacture goods specified under this Directive;

13) "Markings provider", or alternatively and interchangeably, "ID Issuer" or "Company" means a person appointed by the Tax Authority to provide Unique Identifiers for digitized Markings, print and supply excise Markings in an integrated System; install, configure, test, commission, support and maintain the System and do any other things as may be directed by the Tax Authority;

14) "Package" means a packet, bottle or similar wholesale or retail unit of excisable goods specified under this Directive;

15) "Proclamation" means the Excise Tax Proclamation No 1186/2020 ( as amended);

16) "Registry" means the record established and maintained by the Markings provider that issues all the UIs generated for ROs, facilities and machines along with the corresponding information;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

23) በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላት እና ሀረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

17) "Registered Operator", hereafter and interchangeably, RO, means a person who has registered, which is a natural or legal person who is involved as a Licensed Manufacturer, Licensed Importer, Licensed Operator, for the goods subject to Excise Markings specified in Article 3 of this Directive. It also includes Wholesaler or Distributor involved in the trade of excisable products as specified in Article 10 of this Article.
18) "Retailer" shall mean any person or business that sells excisable goods directly to the end consumer and does not typically hold such goods for resale to other retailers.
19) "Tax authority" means the Tax Authority or the Customs Commission, as appropriate;
20) "Time Stamp" means the date and time of occurrence of a particular event recorded in UTC (Coordinated Universal Time) time in a prescribed format.
21) "Unique Identifier" or, interchangeably, "UI", shall mean a numeric or alphanumeric string that is associated with a single unique code to monitor and regulate the production, storage, and movement of excisable goods in Ethiopia.
22) "Wholesaler" shall mean a person that buys excisable goods from one or more Distributors, Importers and Manufacturers, then sells them to other Wholesalers and/or Retailers.
23) Other words and Phrases used in this Directive shall have the meaning ascribed to them under the Proclamation.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## ክፍል ሁለት
## ስለ ኤክሳይዝ ቴምብር

### ३. የኤክሳይዝ ምልክት የሚደረግባቸው እቃዎች

1) የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የኤክሳይዝ ምልክት ሊድረግባቸው ይገባል፤

ሀ) የአልኮል መጠጦች፤

ለ) አልኮል እና አልኮል አልባ ቢራ፤

ሐ) የወይን ጠጅ ወይም የተጣራ አልኮል የታከለበት ወይን ጠጅ እና ተመሳሳይ የአልኮል መጠናቸው ከ0.5% በላይ የሆነ ምርቶች፤

መ) ለሰው መጠጥነት የሚውሉ እና ለመጠጣት ዝግጁ በሆነ መልክ የተመረቱ መጠጦች (ከዚህ በኋላ "ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ መጠጦች" ተብለው የሚታወቁ) በውስጣቸው እንደ ስኳር፤ የፍራፍሬ ጭማቂ፤ የአትክልት ጭማቂ፤ የተፈጥሮ ወይም አርተፊሻል ጣእም ሰጪ ነገር፣ ውሃ፤ የሚኒራል ውሃ፤ ቅጠላ ቅጠል፤ቅመማ ቅመም እና ሌሎች ከአትክልት የሚገኙ ነገሮች ወይም ካርቦንዳዮክሳይድ የተጨመረባቸው እና የአልኮል መጠናቸው ከ0.25 ያላነሰ የአልኮል መጠጦች፤

ሠ) ሲጋራ፣ ትምባሆ፣ በራስ የተጠቀለለ ትንባሆ፣ የሲጋራ ወረቀቶች፣ ቢዲስ፣ ክሬቴክስ፣ ጭስ የሌለው ትምባሆ፣ ሲጋራ፣ ሺሻ፣ የቧንቧ ትምባሆ እና ሌሎች የሚቃጠሉ ወይም የማይቃጠሉ የትምባሆ ምርቶች በሙሉ ለሰው ልጅ ፍጆታ የሚውሉ ሲጋራ እና ሌሎች የትምባሆ ውጤቶች፤

ረ) ከአልኮል መጠጥ ጋር የሚደባለቁትን ጨምሮ (ከዚህ በኋላ " አልኮል የሌለባቸው ስኳር በማጣፈጫነት የተጨመረባቸው መጠጦች" ተብለው የሚታወቁ) አልኮል የሌለባቸው መጠጦች፤ ካርቦን የተጨመረባቸው መጠጦች እና ጣፋጭነት ያላቸው መጠጦች፤

ሰ) ሽቶዎች፤ እና

ሰ) የታሸገ ውሃ

2) ሚኒስቴሩ ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የኤክሳይዝ ምልክት እንዲደረግባቸው ሊወስን ይችላል፡፡

3) የታክሱ ባለስልጣን የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ምልክት አይነት፣ እና በእያንዳንዱ የእቃ ምድብ እና ንኡስ ምድብ ላይ የኤክሳይዝ ምልክት የሚደረግበትን አኳኋን እና የሚደረግበትን ጊዜ ይህ መመሪያ በአስተዳደር ማስታወቂያ (ከዚህ በኋላ " የአስተዳደር ማስታወቂያ" ተብሎ በሚጠራው) ከወጣበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ ያስታውቃል።

## PART TWO

## EXCISE MARKINGS

### 3. GOODS ON WHICH EXCISE MARKINGS SHALL BE AFFIXED

1) Excise Markings shall be affixed on the following excisable alcohol and tobacco goods when imported or produced locally:

a) Compounded spirits,

b) Alcoholic and non- alcoholic Beer,

c) Wines and fortified wines, and other similar products of alcoholic content of more than 0.5%

d) Drink products for human consumption in ready to drink form (hereafter "RTD") in which ingredients such as sugar, fruit juices, vegetable juices, natural or artificial flavoring preparations, water, mineral water, herbs, spices, other botanical substances and/or carbon dioxide are added to alcoholic products, where the volume of alcoholic content is at least 2%.

e) Cigarettes, cigarette tobacco, roll your own tobacco, cigarette papers, beedis, kreteks, smokeless tobacco, cigars, hookahs, pipe tobacco and all other combustible or non-combustible tobacco products for human consumption.

f) Non-alcoholic, carbonated beverages and sweetened beverages, including those intended to be mixed into an alcoholic drink (hereafter, "Non-alcoholic Sugar Sweetened Beverages").

g) Perfumes

h) Bottled water.

2) The Minister may specify other goods on which Excise Markings shall be affixed.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

3) The Tax Authority shall specify the type and the manner of affixing Excise Markings to each category or sub-category of goods, with relevant timelines, by a Administrative Rules Notification (hereafter, "ARN") within 90 days of the effective date of this Directive.

## 4. የኤክሳይዝ ቴምብር ተፈላጊ ባህርያት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚደረገው ማናቸውም አይነት የኤክሳይዝ ምልክት የሚከተሉትን ተፈላጊ ባህሪያት የሚያሟላ መሆን አለበት፤

1) ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ የታክሱ ባላስልጣን በሚያወጣው የአስተዳደር ማስታወቂያ የተመለከተውን ልዩ መለያ የያዘ፤
2) አስመስሎ መስራትን መከላከል የሚያስችል፤
3) በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የኤክሳይዝ ምልክትን እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች መከታተል የሚያስችል፤
4) የተመረቱ ወይም ወደ አገር የገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ምርት ሂሳብ መከታተል የሚያስችል፤
5) በእቃዎች ላይ የሚደረገውን የኤክሳይዝ ቴምብር እና የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ትክክለኛነት በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያለ ማናቸውም ሰው እንዲያረጋግጥ የሚያስችል፤ እና
6) ሲጋራ እና የትምባሆ ቅጠልን በሚመለከት በአለም የጤና ድርጅት ተፈላጊ የሆነውን ምልክት፤

## 4. REQUIREMENTS OF EXCISE MARKINGS

Every excise Marking required to be affixed on excisable goods under Article 3 of this Directive shall fulfil the following specifications:

1) Incorporate a Unique Identifier as specified at in the Administrative Rules Notification to be issued by the Tax Authority within 90 days of the date of issue of this present Directive.
2) deter counterfeiting;
3) facilitate tracking of the Markings and excisable goods along the supply chain;
4) enable accounting for the production of excisable goods manufactured or imported;
5) enable anyone in the supply chain to verify the authenticity of the excise Markings affixed and the excisable goods; and
6) in the case of cigarettes and tobacco products, marking specified under Article 8 of the World Health Organization Protocol to prevent illicit trade of tobacco products.

## 5. የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ እና ክፍያዎች

1) የታክሱ ባለስልጣን የተለየ መለያ የማዘጋጀቱን ተግባር ለዙ አላማ ለሚመረጥ ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ("የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ") በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## 5. EXCISE MARKINGS PROVIDER AND FEES

1) The Tax Authority may, at its own discretion, delegate generation of the UI to an

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

2) የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ መለያው የትለየ መሆኑን የማረጋገጥ እንዲሁም ይተለየ መለያ የማውጣቱ እና የማሰራጨቱ ሂደት፤ ፕሮቶኮል፤ እና አፈጻጸም በከፍተኛ ሚስጥራዊ ደረጃ የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት።

3) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት በወጣው የኤክሳይዝ አስተዳደር መመሪያ መሰረት ፈቃድ የተሰጣቸው አከናዋኞች የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ የተለየ መለያውን ለማውጣት የሚያስችል መረጃ በሚጠይቅበት ጊዜ አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ መስጠት አለባቸው።

4) ፈቃድ የተሰጠው አምራች ወይም አስመጪ በሚያስፈልገው በእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት እቃ ላይ ለሚያደርገው የኤክሳይዝ ምልክት ልክ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው የማስከፈያ ሰንጠረዥ በተመለከተው የማስከፈያ ዋጋ ተመን መሰረት ለኩባንያው ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

5) ለኤክሳይዝ ምልክቶች ክፍያ የሚፈጸመው አምራቹ ወይም አስመጪው የኤክሳይዝ ምልክቱን ከመረከቡ በፊት ነው፡፡

independent third party appointed for these purposes (“Excise Markings provider”).

2) The Excise Markings provider will ensure the uniqueness of the identifier and shall maintain the highest standards of confidentiality with regard to the processes, protocols and practices of the issue and generation of UIs.

3) Licensed Operators licensed under the Directive on Excise Tax Proclamation shall provide all information necessary to the Excise Markings provider issuer when requesting UIs, for the issuer to be able to generate that identifier.

4) Excise Markings fees to be charged on excise Markings needed by the importer or manufacturer for each type of excisable goods shall be paid to the Company as specified in a Schedule to be issued by the Ministry.

5) The excise Markings fees shall be payable before the Markings are issued to the manufacturer or importer.

## 6. የኤክሳይዝ ምልክት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1) የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው እንደሚገባ የተለዩ እቃዎችን የሚያመርት ወይም ወደአገር የሚያስገባ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የኤክሳይዝ ምልክት እንዲሰጠው በጸደቀው ቅጽ ለባለስልጣኑ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከሚመረትበት ወይም ወደአገር ከሚገባበት ቀን ቢያንስ 60 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን መቅረብ አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት አምራች ወይም አስመጪ በታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ15

## 6. APPLICATION FOR EXCISE MARKINGS

1) A licensed manufacturer or importer of excisable goods shall apply to the Tax Authority for excise Markings in the prescribed form.

2) An application for excise Markings in accordance with sub article 1 of this Article shall be submitted to the Tax Authority at

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ቀን ጊዜ ውስጥ ለኤክሳይዝ ምልክት የሚከፈለውን ክፍያ ለምልክቶች አቅራቢው መከፈል አለበት፡፡

4) ማናቸውም አስመጪ ወደአገር በሚያስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የሚደረግ የኤክሳይዝ ምልክት እንዲሰጠው ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር እቃዎችን ወደአገር የሚያስገባ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን ማቅረብ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም የታክሱ ባለስልጣን አስመጪው የኤክሳይዝ ምልክት ሊደረግባቸው የሚገባ እቃዎችን ወደአገር የሚያስገባ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታውን ሳይወጣ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ግዴታ እንዲገባ በማድረግ የኤክሳይዝ ምልክቱን እንዲያገኝ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

6) የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ መሰረት በሚቀርብለት ማመልከቻ ላይ በ5 ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

7) የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ምልክት ሊደረግባቸው የሚገባ ምርቶችን የሚያመርቱ ወይም ወደአገር የሚያስገቡ ታክስ ከፋዮችን ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል።

least sixty days before the manufacture or importation of the excisable goods.

3) A manufacturer or importer of excisable goods shall pay the excise Markings fees to the Markings Provider within 15 days from the date of approval of the application by the Tax Authority.

4) An Importer shall provide evidence that he is importing excisable goods on which excise Markings shall be affixed under this Directive together with the application for excise Markings.

5) Notwithstanding the provisions of sub-article (4) of this article, the Tax Authority may, subject to an undertaking that may be imposed by the Tax Authority, authorize an importer of excisable goods to receive excise Markings before submitting evidence of importation.

6) The Tax Authority shall act on the application within 5 working days from the date in which complete application has been submitted

7) The Tax Authority shall maintain records of taxpayers who produce or import excisable goods on which excise Markings shall be affixed.

## 7. የተለየ መለያ እና የፊዚካል ኤክሳይዝ ምልክቶች አተገባበር

1) የተፈቀደለት አከናዋኝ የኤክሳይዝ ምልክትን ተግባራዊ የሚያደርገው ሀዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሁለት አማራጮች በአንዱ ነው፡-

## 7. IMPLEMENTATION OF UI s AND PHYSICAL EXCISE MARKINGS

1) Licensed Operators may implement the Excise Markings requirement by one of two methods:

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሀ) የተለየ መለያውን የታክሱ ባላስልጣን በሚያወጣው የአስተዳደር ማስታወቂያ በተመለከተው መሰረት በእቃው መያዣ ላይ በማድረግ፤

ለ) በኤክሳይዝ ምልክት አቅራቢው የተዘጋጀውን የፊዚካል የቴምብር ምልክት በመረከብ ይህንን ምልክት በገቢዎች ሚኒስቴር በሚወጣ የኤክሳይዝ ቁጥጥር መመሪያ በተመለከተው መሰረት በእቃው መያዣ ላይ በመለጠፍ፤

2) ፈቃድ የተሰጠው አምራች ወይም አስመጪ የአስተዳደር ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ በጀመረ በ60 ቀናት ጊዜ ውስጥ ከሁለቱ በቀደመው ጊዜ ፤ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከትመለከቱት በአንዱ ለመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ማቅረብ አለበት። የዚህ አይነቱ ማመልከቻ በአስተዳድር ማስታወቂያ በሚገለጸው ቅጽ መሰረት በጽሁፍ የሚዘጋጅ ሆኖ አንላይን ወይም በካል መቅረብ አለበት።

a) Directly printing UIs on product packaging in accordance with the guidelines provided by the Tax Authority in a Notification to be issued.

b) Acquiring physical Excise Markings printed by the appointed Excise Markings provider and affixing them to products in accordance with the guidelines provided by the Tax Authority in under the Excise Control Directive

2) Licensed Manufacturers and Importers must, within 60 days of the issue of the required Notifications under this Directive, or within 60 days of commencing business in Ethiopia, whichever is later, apply to the Tax Authority for authorization for one of the above two options at sub-article (1) . Application must be made in writing and submitted online or physically, on the form to be provided in the ARN.

## 8. የኤክሳይዝ ምልክት ከማድረግ ነጻ ስለመሆን

1) በዚህ መመሪያ የተመለከተው ቢኖርም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች የፊዚካል ቴምብር ወይም የተለየ መለያ ከማድረግ ግዴታ ነጻ ተደርገዋል፦

ሀ/ ልዩ መብት ለተሰጣቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለሚሸጡ የቀረጥ ነጻ መደብሮች እንዲውሉ ወደአገር የሚገቡ ወይም ከአገር ውስጥ የሚገዙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች፤

ለ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እቃዎች፤

ሐ) በኢትዩጵያ በኩል በትራንዚት የሚያልፉ እቃዎች፤

መ) በአለምአቀፍ የፖስታ አገልግሎት በኩል የሚያልፉ ብዛ ከንግድ መጠን በታች የሆነ እቃዎች፤እና

ሠ) በናሙናነት ወደአገር የሚገቡ የኤክሳይዝ የሚከፈልባቸው እቃዎች፤

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) የተዘረዘሩት የኢክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና

## 8. EXEMPTION FROM EXCISE MARKINGS

1) Notwithstanding the provisions of this Directive, the following excisable goods shall be exempted from the requirement of printed excise markings or UIs implemented on product packaging:

a. excisable goods imported or purchased for supply to a duty free shop which sales such goods to privileged persons or institutions;
b. goods destined for export;
c. goods on transit through Ethiopia,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ደንብ በተመለከተው መሰረት “ ከቀረጥ ነጻ” የሚል ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል።

3) የታክሱ ባለስልጣን ተጨማሪ ማስታወቂያ በማውጣት ፈቃድ የተሰጣቸው አስመጪዎች እና አምራቾች ከኤክሳይዝ ምልክት ነጻ የተድረጉትን እቃዎች በሚመለከት በየጊዜው ሪፖርት እንዲቀርብለት ለመጠየቅ ይችላል።

d. goods below a commercial quantity imported through international postal service; and

e. Excisable goods imported into Ethiopia as samples.

2) Excisable Goods under sub-article 1 (a) of this Article shall be marked “ Duty Free” as provided under Excise Tax Proclamation and Council of Ministers Customs Regulations. .

**3)** The tax authority shall, by further notice, require licensed importers and manufacturers to provide periodic reports on goods exempted from excise marking requirements.

## 9. ከቀረጥ ነጻ በተደረጉ እቃዎች እና ማሸጊያዎች ላይ ስለሚደረግ ምልክት

1) በአዋጁ የተመለከቱ ከቀረጥ ነጻ የተደረጉ ወይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እቃዎችን ለመለየት እና ለመከታተል እንዲቻል የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል።

2) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1አፈጻጸም ለጅምላ ሽያጭ በሚቀርበው እቃ መጠቅለያ ላይ የሚከተለ ምልክት ሊታተም ይገባል፦

ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡትን በሚመለከት የመጨረቻ መዳረሻ የሆነውን አገር ስም፤

ለ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉትን እቃዎች በሚመለከት “ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል”

ሐ) በቀረጥ ነጻ መደብሮች ውስጥ የሚሸጡትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች በሚመለከት “ ከቀረጥ ነጻ”።

## 9. MARKING OF DUTY FREE PRODUCTS AND PACKAGES

1) All packages of duty free or export excisable goods specified in the Proclamation shall bear distinct markings to enable the goods to be trackable and traceable.

2) For the implementation of sub-article (1) of this Article, the material wrapping the package for wholesale purposes shall have printed on it:

a. in the case of exports, the country of final destination;

b. in the case of excisable goods for consumption in Ethiopia, "FOR USE IN ETHIOPIA";

c. in the case of excisable goods for sale to duty-free shops, "DUTY FREE";

## 10. የተመዘገቡ አከናዋኞች ስርአት

1) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 15(1) (መ) በተደነገገው መሰረት በአልኮል እና ትምባሆ ውጤቶች

## 10.REGISTERED OPERATOR (RO) SYSTEM

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

የጅምላ ንግድ እና የማከፋፈል ስራ ላይ ለተሰማሩ "የተመዘገቡ አከናዋኞች" ስርአት በዚህ መመሪያ ተመስርቷል። በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በተመለከተው መሰረት ማናቸውም በአልኮል መጠጥ እና በትምባሆ ንግድ ስራ ላይ መሰማራት የሚፈልግ ሰው በገቢዎች ሚኒስቴር በተዘጋጀው የኦንላይን መዝገብ ላይ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት።

2) የዚህ አይነቱ ምዝገባ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው መሰረት የአስተዳደር ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን አንስቶ በ90 ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት። የተመዘገቡ አከናዋኞች የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሲሆን፤ የምስክር ወረቀቱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ስራ በሚያከናውኑበት በሁሉም ስፍራ በሚታይ ቦታ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው።

3) በገቢዎች ሚኒስቴር ፈቃድ የተሰጣቸው የአልኮል ማጣሪያዎች፤ፈቃድ የተሰጣቸው የአልኮል እና የትምባሆ ውጤቶች አምራቾች እንዲሁም በአልኮል እና በትምባሆ ውጤቶች የጅምላ ንግድ እና የአከፋፋይነት ስራ ላይ የተሰማሩ የተመዘገቡ ሰዎች ከጥር 1 ቀን 2025 ብዚህ መመሪያ መሰረት እንደተመዘገቡ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ በፋብሪካ ወይም በአስመጪ የስራ ቦታ የተቋቋመ የችርቻሮ መደብር በተለይ መመዝገብ አለበት።

4) በዚህ መመሪያ መሰረት  የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት የመያዝ ግዴታ ተፈጻሚ የሚሆነው  ለጅምላ ሻጮች እና አከፋፋዮች ብቻ ነው።

5) በአልኮል እና በትምባሆ ምርቶች የጅምላ ንግድ እና አከፋፋይነት ስራ ላይ ለተሰማራ የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የሚችለው በአስተዳደር ማስታወቂያ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው። ይሁን እንጂ በኦንላይን ምዝገባ ላከናወነ ሰው ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ሲሆን፤ በማከታተል የታክሱ ባላስልጣን የኤክሳይዝ ባለሙያ የምዝገባውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት።

6) የታክሱ ባላስልጣን የንግድ ስራው የሚከናውንበትን ቦታ አግባብነት ጨምሮ ሌሎችም ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ዋንኛውን የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት ይሰጣል። የዚህ አይነቱ የማረጋገጥ ስራ ጊዜያዊ የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት በተሰጠ በስድስት ወር ወይም የታክሱ ባላስልጣን በሚወስነው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መከናወን አለበት።

7) የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት የሚሰረዘው አግባብነት እስካለው ድረስ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የተፈቀደለት አምራች ወይም አስመጪ ፈቃድ ሰለሚሰረዝበት ሁኔታ በተደነገገው መሰረት ይሆናል።

1) A "Registered Operator" (hereafter, "RO") system is hereby introduced under the powers at Art. 15(1)(d) of the Excise Proclamation for distributors and wholesalers of alcoholic and tobacco products.. All persons wishing to carry on a trade or business in alcoholic and tobacco goods as defined by the Excise Proclamation shall apply for registration on the online portal of the Tax Authority.
2) Such registration must be undertaken within 60 days of the issue of the ARN specified at sub-article 3 of this Article or Article 3 of this Directive. Registered operators will be provided with an appropriate certificate to that effect, which must be displayed at a prominent position at each location where such trade in specified excisable goods is undertaken.
3) All persons licensed by the Tax Authority as a Licensed Distiller, Licensed Manufacturers of alcoholic and tobacco products, and Registered as person engaged in the Distribution or Wholesale business for alcoholic and tobacco goods as of 8 January 2025 shall be deemed to be registered by virtue of this Article. However, any retail outlet at factory or importer premises shall be subject to separate registration.
4) The requirement to obtain an RO Certificate shall be further restricted to Distributors, Wholesalers of alcoholic and tobacco goods.
5) Every RO certificate as a Distributor or a Wholesaler in alcoholic beverages and tobacco goods shall be subject to fulfillment of the conditions for such trade as specified in the ARN. The relevant RO certificate will

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

be provisionally issued on online registration and shall be subject to endorsement by the senior officer of excise officer of the Tax Authority .

6) The Tax Authority shall, after it is satisfied that the prescribed conditions are met, including the fitness of the said premises, endorse the relevant RO certificate. Such endorsement processes shall be carried out within six month of issue of the RO certificate, or such longer time that the Minister of Revenue may allow.

7) Cancellations of such RO certificates shall be subject to such rules as specified in the Excise Tax Proclamation for cancellation of licenses issued for manufactures and importers, as appropriate.

**11. የኤክሳይዝ ምልክት የተደረገባቸውን የተወሰኑ እቃዎች በመጋዘን ለመያዝ ወይም መልሶ ለመሸጥ የተመዘገበ አከናዋኝ የምስክር ወረቀት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ**

1) የሚከተሉትን እቃዎች መልሶ ለመሸጥ ወይም ለቸርቻሪዎች ለማከፋፈል መያዝ የሚችሉት የተመዘገበ አከፋፋይ ወይም ጅምላ ሻጭ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ናቸው፡-

ሀ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (እንደተሻሻለው) በተተረጎመው መሰረት የአልኮል ምርቶች፤

ለ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (እንደተሻሻለው) በተተረጎመው መሰረት የትምባሆ ምርቶች፤

2) የታክሱ ባላስልጣን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተዘረዘረው ላይ ተጨማሪ ምድቦችን ሊያካትት ይችላል።

3) የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ምልክት ተደርጎባቸው በመጋዘን የተያዙትን የሚያሳየውን ጨምሮ፤የታክሱ ባላስልጣን በሚያወጣው አስተዳደራዊ ማስታወቂያ መሰረት የሂሳብ መዝገብ እና ሰነዶችን በተፈቀደለት የስራ ቦታ መያዝ አለበት።

**11.RO CERTIFICATE NECESSARY TO HOLD CERTAIN GOODS WITH EXCISE MARKINGS FOR STORAGE AND RESALE.**

1) Only RO’s certified as Distributors and Wholesalers may hold the following goods for further resale or distribution to Retailers:

   a. All alcoholic products within the definition of such goods in the Excise Proclamation, as amended.

   b. All tobacco products within the definition of such goods in the Excise Proclamation, as amended.

2) The Minister of Revenue may add further categories to sub Article (1)of this Article

3) The licensee shall keep on the licensed premises such books and records, and maintain such other controls, including

the storage of goods with Excise Markings, as the Tax Authority may by writing issue in the ARN.

## 12. የኤክሳይዝ ምልክት ፍጆታን አስቀድሞ ስለማስታወቅ

የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራቾች እና አስመጪዎች ቢያንስ የኤክሳይዝ ምልክቱን ከሚፈልጉበት ወር የመጀመሪያ ቀን በፊት ካሉት 60 ቀናት በፊት ለስድስት ተከታታይ ወራት በየወሩ የሚያስፈልጋቸውን የኤክሳይዝ ምልክት ብዛት ግምት እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፡ ፡

## 12. SUBMISSION OF EXCISE MARKINGS CONSUMPTION FORECAST

The Tax Authority may require a manufacturer or importer of excisable goods to provide, at least sixty days before the beginning of the month in which the manufacturer or importer will require the Markings, a forecast of the quantities of excise Markings which the manufacturers or importer intends to use in each month for the subsequent period of six months.

## 13. ኩባንያን ስለመምረጥ

1) ሚኒስቴሩ በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት በወጣው መመሪያ ሰለግዢ አፈጻጸም የተዘረጋውን ስርአት በመከተል የሚከተሉትን ተግባራት የሚያከናውን ኩባንያ ይመርጣል፤
   ሀ) በገቢዎች ሚኒስቴር በሚወሰን ቦታ ተፈላጊ የሆነውን ደረጃ የሚያሟላ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የተለየ መለያን የሚያለማ፤የሚተክል እና የሚያስተዳድር;
   ለ) የተፈቀደላቸው አከናዋኞች የሚጠቀሙበትን አግባበነት ያለውን ስርአት የሚያለማ እና የሚተክል፤
   ሐ) ፊዚካል የቴምብር ምልክቶች የሚታተሙበትን አንድ የማተሚያ ተቋም ጨምሮ የታክሱ ባላስልጣን የሚያስፈልገውን ተዛማጅ ስርአት የሚተክል፤
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመረጠው ኩባንያ በታክስ ባለስልጣኑ ካልታዘዘ በስተቀር በዚህ መመሪያ የተመለከተውን ማናቸውንም አይነት የኤክሳይዝ ምልክት ለማተም አይችልም፡፡
3) በኩባንያው እና በገቢዎች ሚኒስቴር መካከል የሚፈረመው ውል ከሌሎች መካከል ኩባንያው ፡-

## 13. PPOINTMENT OF A COMPANY

1) The Ministry following the procedures laid down under Public Procurement and Property Administration Proclamation and Directives issued thereunder, shall appoint a Company/companies to carry out the following activities :
   a) to develop, install and maintain a System that generates UIs with the required standard of integrity and security at the designated premises of the Tax Authority;
   b) to develop and install components of the System relevant to licensed ROs; and
   c) to install any other related systems required by the Tax Authority,

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሀ) በውሉ መሰረት ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሚያገኘውን የታክስ ከፋዮችን ሚስጥር መጠበቅ እንዳለበት እና ለዚህ የውል ግዴታ አፈጻጸም የታክሱ ባላስልጣን ኩባንያው ቦንድ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያስይዝ ሊጠይው እንደሚችል፤

ለ) የተለየ መለያ ሊያለማ ወይም የኤክሳይዝ ምልክቶችን ሊያትም የሚችለው በገቢዎች ሚኒስቴር ሲታዘዝ እና በውሉ በተመለከተው የአሰራር ስርአት መሆን እንዳለበት፤

ሀ) የተለየ መለያ የሚሰራጨው የአስተዳድር ማስታወቂያውን መሰረት በማድረግ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በሚደረግ ስምምነት በሚወሰን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፕሮቶኮል እና ስርአት መሰረት ሊሆን እንደሚገባ፤

4) የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ ገለልተኛ ሆኖ መስራት ያለበት ሲሆን፤ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ንኡስ የስራ ተቋራጮችን ማስታወቅ እና በአስተዳደር ማስታወቂያው የተመለከቱ አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

5) የኢክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ በማቸውም ጊዜ የሚከተሉትን የሚያካትት ስራውን የሚያጠናቅቅበት እቅድ ሊኖረው ይገባል፡-

ሀ) ስራውን የሚረከብ ሌላ ኩባንያ የሚመረጥ ቢሆን፤ አዲሱ አቅራቢ ስራውን እስከሚረከብ ድረስ የአልግሎት አሰጣጡ ሳይቋረጥ የሚቀጥል ለመሆኑ ዋስትና የሚሆን የአሰራር ስርአት መዘርጋት፤

ለ) ይህንን ስርአት በገቢዎች ሚኒስቴር ማስጸደቅ፤

including a single printing facility for printing of any physical Excise Markings..

2) The Company appointed under paragraph (1) shall not print any excise Markings required under this directive unless requested by the Tax Authority to do so.

3) The Contract to be signed between the Tax Authority and the Company shall, among others, specify that the company shall

a. maintain the confidentiality of business secrets of taxpayers which he has acquired during the performance of the contract. the Tax Authority may require the posting of an appropriate bond or other security to that end.

b. That it only generates UIs and prints excise markings under prior authority issued by the Tax Authority , through processes to be agreed in the contract.

c. UIs will be issued in accordance with the Information Communication Technology protocols and systems agreed with the Tax Authority, following the guidelines at the TSN.

4) The Excise Markings provider shall be independent, will disclose all subcontractors necessary for the performance of its functions and will comply with the criteria set out in the relevant Paragraph of the TSN.

5) The Excise Markings provider must at all times have in place an exit plan:

a. That establishes the procedure to be followed to guarantee the continuity

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

of the operation of the service, in the event that a successor entity is to be appointed to carry out the service, until the new provider is appointed.

b. That has been approved by the Tax Authority.

## 14. የኤክሳይዝ ቴምብርን ስለማስረከብ

1) የታክስ ባለስልጣኑ የሚያስቀምጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የታክስ ባለስልጣኑ ኩባንያው በባለስልጣኑ የተዘረጋውን የአሰራር ስርአት በመከተል የኤክሳይዝ ምልክቶችን እንዲያትም እና በቀጥታ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው እንዲያስረክብ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ኩባንያው የኤክሳይዝ ምልክቶችን በሚመለከት ከታክስ ባለስልጣኑ የተቀበለውን ትዕዛዝ በ10 (አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

3) የኤክሳይዝ ምልክቶችን እንዲያቀርብ የተመረጠው ኩባንያ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ያከፋፈለውን የኤክሳይዝ ምልክት አይነት እና ብዛት የሚያሳይ መረጃ የታክስ ባለስልጣኑ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን መስጠት አለበት፡፡

4) የኤክሳይዝ ምልክቶች አቅራቢ የተለየ መለያን የሚያሰራጨው ከአቅራቢው ጋር በተደረገ ውል በተመለከተው ስርአት መሰረት የተለየ መለያው በገቢዎች ሚኒስቴር ሲጸድቅ ይሆናል።

5) የታክስ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት አምራቾች እና አስመጪዎች የወሰዱትን የኤክሳይዝ ቴምብር አጠቃቀም ትክክለኝነት በመከታተል ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 14.DELIVERY OF EXCISE MARKINGS

1) The Tax Authority may, subject to such conditions as the Tax Authority may impose, instruct the Company to print excise Markings and deliver the Markings directly to a manufacturer or importer of excisable goods following the procedures laid down by the Tax Authority..
2) The Company shall deliver the Markings in accordance with the instruction given pursuant to Article 1 of this Article within 10 ( ten) working days .
3) The Company appointed to produce excise Markings shall notify the Tax Authority of the quantity and type of excise Markings supplied under paragraph (1) within such period as the Tax Authority may require.
4) The Markings provider shall only issue UIs, after approval of the relevant batch of UIs by the Ministryof Revenue, through processes to be agreed and implemented on award of the contract to the Markings provider.
5) The Tax Authority shall ensure that manufacturers and importers use the excise

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

Markings for its intended purposes properly and take measures on irregularities.

## 15. የኤክሳይዝ ምልክት የሚደረግበት ጊዜ እና ቦታ

1) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ምልክት የሚደረገው የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው መሰረት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፡

   ሀ) በአገር ውስጥ በሚመረቱ እቃዎች ላይ በማምረቻ ቦታው ምርቱ እንደታሸገ ወዲያውኑ፤

   ለ) ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ፤

      i) በጉምሩክ ጣቢያ፤ወይም
      ii) የጉምሩክ ፎርማሊቲ በተጠናቀቀ በ 5 ቀናት ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው ቦታ፤

   ሐ) በዚህ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) የተመለከተው ቢኖርም የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደአገር በሚገቡ እቃዎች ላይ ከአስተዳደር ማስታወቂያው ጋር በተጣጣመ አኳሗን የኤክሳይዝ ምልክት እቃዎቹ በሚላኩበት አገር በሚገኝ የማምረቻ ቦታ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡ ፡

2) የታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት በእያንዳንዱ መያዣ ላይ ከአስተዳድር ማስታወቂያው ጋር በጣጣመ ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ምርት ምንነት ለማወቅ፤ ምርቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር እና የተመረተውን ምርት ሂሳብ ለመመዝገብ የሚያስችል ሊታይ በሚችል ቦታ ሊጠፋ በማይችል ቀለም የዲጂታል ምልክት እንዲታተምበት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

3) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርት ወይም ወደአገር የሚያስገባ ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች ወይም በመያዣው ላይ የኤክሳይዝ ምልክቱን እንዳደረገ ወዲያውኑ የአስተዳደር ስርአቱን በመጠቀም ይህንኑ ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

## 15. PLACE AND TIME OF AFFIXING EXCISE MARKINGS

1) Excise Markings shall be affixed on excisable goods in the manner specified by the Tax Authority in the following manner:-

   a) in case of locally manufactured goods, at the production facility immediately after packaging;
   b) in the case of imported goods:
      i) at the customs post; or
      ii) at a place determined by the Tax Authority within five days of the clearance for importation of the goods:
   c) Notwithstanding the provisions of (b) of this article, the Tax Authority may allow excise Markings on imported excisable goods to be affixed at the production facility in the exporting country in accordance with such conditions as the Tax Authority may specify, consistent with the requirements of the TSN..

2) The Tax Authority may, upon the application, permit digital Markings to be printed by the System on each package and in a visible place with indelible security ink to enable the authentication of, tracking and tracing of, and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

4) ይህንን መመሪያ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማናቸውም ሰው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ይቀጣል፡፡

## 16. የኤክሳይዝ ቴምብርን ተመላሽ ስለማድረግ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸን እቃዎች የሚያመርት ወይም ወደአገር የሚያስገባ ማናቸውም ሰው ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም የተረከበውን የኤክሳይዝ ምልክት ለታክሱ ባለስልጣን ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሀ) አምራቹ የማምረት ስራውን ሲያቋርጥ፤

ለ) የኤክሳይዝ ቴምልክቱ ወረቀት ወይም ጥቅሉ ብልሽት ያለበት ከሆነ፤

ሐ) ማስታወቂያ በቀረበበት ወደአገር በሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ እና ወደአገር መግባቱ በተረጋጠው እቃ መካከል ልዩነት ያለ ሲሆን፤

መ) የታክስ ባለስልጣኑ የኤክሳይዝ ምልክቱ ጥቅም ላይ እንዳይውል የወሰነ እንደሆነ፤ ወይም

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት እቃ የኤክሳይዝ ምልክት ከሚደረግባቸው እቃዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲወጣ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ የተወሰነ ከሆነ፤

2) ኩባንያው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ)እና (ሐ)ከተመለከተው በስተቀር የኤክሳይዝ ምልክቱ ተመላሽ ከተደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 90 ቀናት ጊዜ ውስጥ አምራቹ ወይም አስመጪው

production accounting for excisable goods, consistent with the requirements of the TSN.

3) A manufacturer or importer of excisable goods shall declare in the System the excise Markings used immediately after affixing on the excisable goods or the package containing excisable goods.

4) A person who contravenes the provisions of this Directive commits an offence and shall be liable on conviction to a penalty provided under the Excise Tax Proclamation or the Tax Administration Proclamation.

## 16. RETURN OF EXCISE MARKINGS

1) A manufacturer or an importer of excisable goods shall return the unused excise Markings to the Tax Authority upon the occurrence of the following:

a) the manufacturer stops manufacturing;

b) there are defects in the excise Markings sheets or reels;

c) there is a discrepancy between the declared and the verified imports of the excisable goods;

d) the excise Markings have been declared out of use by the Tax Authority; or

e) the excisable goods have been excluded from the requirements of this Directive by the Ministry.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ለመለሰው የኤክሳይዝ ምልክት የከፈለውን ክፍያ መመለስ አለበት፡፡

2) The Company shall refund to the manufacturer or the importer of excisable goods, as the case may be, the excise Markings fees paid for excise Markings returned except those specified in sub-article 1(a) and (c) within thirty days of the return of the Markings.

## 17. የተበላሹ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው የኤክሳይዝ ምልክቶች

1) ብልሽት የደረሰባቸው የኤክሳይዝ ምልክቶች የታክስ ባለስልጣኑ ብልሽቱን እስከሚያረጋግጥ ድረስ ተይዘው መቆየት አለባቸው፡፡ ባለስልጣኑ የተበለሹ ወይም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ሲያረጋግጥ የባለስልጣኑ ተወካይ በተገኝበት እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ በታክሱ ባለስልጣን ትእዛዝ የተረከባቸውን የኤክሳይዝ ምልክቶች ሂሳብ ማወራረድ ያልቻለ እንደሆነ ያልተወራረደውን የኤክሳይዝ ምልክት በሚመለከት የታክሱ ባለስልጣን እንደአግባብነቱ አምራቹ ወይም አስመጪው ባመረታቸው ወይም ወደአገር ባስገባቸው እቃዎች ላይ በእቃዎቹ ምድብ ውስጥ ያለውን ከፍተኛውን የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ፤ የእቃዎቹን ዋጋ እና የእቃዎቹን ብዛት መሰረት በማድረግ የኤክሳይዝ ታክሱን እና ሌሎች ታክሶችን አስልቶ ያስከፍላል፡፡

3) የታክሱ ባለስልጣን ያልተወራረደውን የኤክሳይዝ ምልክት ስሌት በሚያከናውንበት ጊዜ ለተበለሹ ወይም ጉዳት ለደረሰባቸው የኤክሳይዝ ምልክቶች ማካካሻ መፍቀድ ያለበት ሲሆን፤ በዚህ አይነት የሚፈቀደው ማካካሻ አምራቹ ወይም አስመጪው ከተረከበው የኤክሳይዝ ምልክት 1% በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

## 17. WASTAGE OR DAMAGE OF EXCISE MARKINGS

1) Damaged excise Markings shall be preserved for verification by an authorized officer. Wastage or damage of excise Markings shall after verification by the Tax Authority be destroyed in the presence of the representative of the Tax Authority.

2) Where a manufacturer or importer of excisable goods cannot account for any excise Markings received based on the authorization of the Tax Authority, the Tax Authority shall compute the excise duty and other taxes on the unaccounted Markings based on the highest excise rate imposed on such category of goods, value and volume of excisable goods manufactured or imported by the manufacturer or importer, as the case may be.

3) In computing excise duty in the case of unaccounted for excise Markings, the Tax Authority shall allow for wastage and

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

damages which shall not exceed one percent of the quantity of the issued Markings.

## 18. የኤክሳይዝ ቴምብርን ስለማስተላለፍ

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች አምራች ወይም አስመጪ በታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ ሲፈቀድለት በእጁ የሚገኘውን የኤክሳይዝ ምልክት በባለቤትነቱ ስር ለሚገኝ ለሌላ አምራች ወይም አስመጪ ዘርፍ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

2) የታክስ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የኤክሳይዝ ምልክት የሚተላለፍበትን ስርዓት እና የሂሳቡን አመዘጋገብ ይወስናል፡፡

## 18. TRANSFER OF EXCISE MARKINGS

1) A manufacturer or importer of excisable goods may, with the prior approval of the Tax Authority, transfer excise Markings held in stock by the manufacturer or importer to another manufacturing or importing unit owned by the same manufacturer or importer.
2) The Tax Authority shall prescribe the procedure and conditions for the transfer and accounting of excise Markings to be made in accordance with sub-article 1 of this Article.

## 19. የሂሳብ መዝገቦችን ስለመያዝ

ፈቃድ የተሰጣቸው አምራቾች ወይም አስመጪዎች የኤክሳይዝ ምልክቶችን ከኩባንያው ከተረከቡ በኋላ የሚከተሉትን መዝግበው መያዝ አለባቸው፤

ሀ/ ባለፈው ወር መጨረሻ ቀን ድረስ በጅ የሚገኙ እና በጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉትን ምልክቶች መጠን ማጠቃለያ፣

ለ/ በአንድ ወር ውስጥ ከኩባንያው የተረከቡዋቸውን ምልክቶችን መጠን ማጠቃለያ ሪፖርት፣

ሐ/ በአንድ ወር ውስጥ ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት የተበላሹ የታተሙ ምልክቶችን ብዛት እና አይነት፣

መ/ ጥቅም ላይ የዋሉ ምልክቶችን እና የተከፈለውን ወይም ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ማስታረቂያ ፣

## 19. MAINTENANCE OF RECORDS

Licensed ROs that are Importers and Manufacturers shall maintain the following records of excise Markings after collecting the Markings from the Company:

a) Consolidated reports of number and type of excise Markings at hand on the last day of the month preceding and Markings utilized in the same month.
b) Consolidated reports of the number and type of excise Markings received in a particular month;
c) Number and type of printed Excise Markings damaged during utilization process.
d) Reconciliation of net markings used and excise taxes paid or payable.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## ክፍል ሶስት
## የኤክሳይዝ ምልክቶች የአስተዳደር ስርአት

### 20. የአስተዳደር ስርአት ስለመዘርጋት

1) በዚህ መመሪያ የተመለከተው ፈቃድ የተሰጠው አከናዋኝ እንደሁኔታው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሚያመርትበት ወይም ወደአገር ያስገባቸውን እቃዎች በሚያከማችበት ቦታ የአስተዳደር ስርአት የሚዘረጋበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለዚህ ተግባር የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን አለበት፡
2) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚዘረጋው የአስተዳደር ስርአት የሚከተሉትን የሚይዝ መሆን አለበት፡
   ሀ) ለስርአቱ የሚያገለግለውን የተለየ መለያ ለማስተዳደር የሚያስችል ሶፍትዌር እና ተፈላጊው ስርአት፤
   ለ) የምልክቱን የተለየ መለያ ትክክለኛንት ለማረጋገጥ እንዲቻል መለያውን ማንበብ የሚያስችል የተንቀሳሽ ስልክ መተግበሪያ እና ሌሎች መተግበሪያዎች፤
   ሐ) የምርት ሂሳብን ለመመዝገብ አስፈላጊ የሆነ መሳሪያ፤ ካለ፤እና
   መ) ለስርአቱ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ የታክሱ ባላስልጣን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለመቆጣጠር፤ ለመመዝገብ እና መረጃዎችን ለማስተላለፍ ለሚያከናውነው ተግባር የሚውል መሳርያ፤
3) በዋንኛው የዳታ ማእከል እና በገቢዎች ሚኒስቴር የመጠባቂያ ማእከል የስርአቱ አካል የሆኑ መሳሪያዎችን የመትከል፤ የማጣጣም፤ ከጥቃት የመከላከል እና የማስተካከያ ጥገና ተግባር ሊከናወን የሚችለው ሃላፊነት በተሰጠው የታክሱ ባላስልጣን ባለሙያ ቁጥጥር ስር ነው።
4) አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በተመዘገበ አከናዋኝ የስራ ቦታ የተከላ፤ የማጣጣም፤ የመከላከል እና የማስተካከል ተግባር የሚከናወነው በተመዘገበው አከናዋኝ ወጪ ነው።

## PART THREE
## EXCISE MARKINGS MANAGEMENT SYSTEM

### 20. INSTALLATION OF THE SYSTEM

1) Licensed ROs specified in this Directive shall facilitate the installation of the System in their premises used for the manufacture, storage of imports, distribution and wholesale of excisable goods, as the case may be, at its own cost.
2) The System to be installed in accordance with this Article shall be composed of:
   (a) Software and system requirements for the management of UIs for the system
   (b) Mobile and other applications needed for verification of the UIs for the markings
   (c) Production accounting equipment required, if any; and
   (d) Devices for the control, registration, recording and transmission of data on quantities of excisable goods which have been subject to marking to the Tax Authority if required by the System.
3) The installation, integration, preventive and corrective maintenance procedures of all the equipment comprising the System at the main data center and disaster recovery centre of the Tax Authority shall be done under the supervision of an authorized officer of the Tax Authority.
4) The installation, integration, preventive and corrective maintenance procedures at any RO's premises, if required, shall be at the expense of the RO.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

## 21. የኤክሳይዝ ምልክት አስተዳደር ስርአት– ማልማት እና ቁጥጥር

1) የታክሱ ባላስልጣንየሚከተሉት ሃላፊነቶች ይኖሩበታል፡-

**ሀ)** በአስተዳደር ማስታወቂያ በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ምልክቶችን የሚያለማው የምልክቶች አቅራቢ ሊከተለው በስራው፤ በደህንነት፤እና በፊስካል ቁጥጥር ረገድ ሊከተለው የሚገባውን አሰራር መወሰን፤

**ለ)** ስርአቱን በመዘርጋት ሂደት ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፤

2) የተለየ መለያን ለማስተዳደር የሚያስፈልገው ሶፍትዌር በገቢዎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥመገጠም ያለበት ሲሆን፤ተገቢው መተግበሪያ እና የአስተዳድር ሶፍትዌር ሞጁል ለሁሉም አምራቾች እና አስመጪዎች ክፍት መደረግ አለበት።

3) የአስተዳደር ስርአቱ አካል የሆነው መሳሪያ በሚከተሉት ቦታዎች መገጠም አለበት፡-

ሀ) በአምራቹ የስራ ቦታ ከሚገኝ ከእያንዳንዱ የማሸጊያ ማሳሪያ ወይም የማተሚያ መሳሪያ ጋር በተያያዘው የማምረቻ መስመር፤

ለ) በገቢዎች ሚኒስቴር ውስጥ በሚገኘው ዋንኛ የመረጃ ማእከል እና የአደጋ መጠባበቂያ ማእከል፤

ሐ) ወደአገር የሚገቡ እቃዎችን ለማስተዳደር የሚውለው ስርአት የታክሱ ባላስልጣን በሚወስነው አኳኋን፤

4/ ስርአቱ በሚተከልበት ጊዜ የተመዘገቡ አከናዋኞች የማምረቻ መስመሮች በትክክል የሚሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

## 22. የአስተዳደር ስርአቱን ለማሻሻል ወይም በአዲስ ለመተካት ስለሚሰጥ ማስታወቂያ

## 21. EXCISE MARKINGS MANAGEMENT SYSTEM - DEVELOPMENT AND SUPERVISION

1) The Tax Authority shall be responsible for:
   a. Defining the functional, security and fiscal control requirements to be observed by the Markings Provider in developing the System as set out in the TSN;
   b. Supervising and monitoring the process of installing the System.
2) Software required for the management of the UIs compliant with the TSN shall be installed in the Ministry of Finance premises and appropriate application and management software modules will be made available for all manufacturers and importers of excisable goods.
3) Equipment that may be a part of the Management System shall be installed;
   a. on all production lines at the manufacturer’s premises corresponding to each packaging machine or labelling machine, if appropriate;
   b. at the main data centre and disaster recovery centre of the Tax Authority;
   c. The System for the management of imports shall be installed in the manner specified by the Tax Authority
4) During the installation of the System, the RO shall ensure that the production lines are in proper operating condition.

## 22. NOTICE OF A NEW OR MODIFIED SYSTEM

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

1) አዲስ ወይም የተሻሻለ የአስተዳደር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን አዲሱ ወይም የተሻሻለው የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ ከሚውልበት ቀን ቢያንስ 30 ቀን አስቀድሞ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፤

ሀ) አዲሱን ወይም የተሻሻለውን የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች፤

ለ) በእያንዳንዱ የምርት ሂደት ላይ ሊደረግ የሚገባውን የማጣጣም ስራ፤

ሐ) የአስተዳደር ስርአቱ አካል ሆነው የሚገጠሙ እና ስራ ላይ የሚውሉ ኮምፒውተሮች እና ሌሎች መሳሪያዎች የሚገጠሙበትን እና ስራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ፤

መ) አዲሱ ወይም የተሻሻለው የአስተዳደር ስርአት ስራ ላይ የሚውልበትን ቀን፤

2) የተመዘገቡ አከናዋኞች የኤክሳይዝ ምልክትን ስራ ላይ ለማዋል፤ ለማሻሻል ወይም ለማጣጣም ለሚውሉ መሳሪያዎች እንዲሁም በእያንዳንዱ የማምረቻ መስመር መሳሪያዎቹ ለሚገጠሙባቸው ቦታዎች የሚያስፈልገውን ወጪ ይሸፍናሉ፡፡

3) የተመዘገበ አከናዋኝ በመሳሪያዎች ላይ ማስተካከያ እንዲያደርግ ወይም አዲስ ወይም የተሻሻሉ መስሪያዎች ለመግጠም የሚያሰፈልገውን መረጃ እንዲሰጥ በታክሱ ባለስልጣን ሲጠየቅ ማስተካከያውን ማድረግ ወይም አዲሱ ወይም የተሻሻለው ስርአት ከሚገጠምበት ቀን ሰባት ቀናት አስቀድሞ መረጃውን መስጠት አለበት፡፡

1) Where a new or modified System is required, the Ministry shall notify the licensed ROs in writing at least ninety days before the installation and integration of the new or modified System and the notice shall state—

(a) the requirements for the equipment to facilitate use of System;

(b) the adaptive features required, on each production line;

(c) the connectivity features and operating environment for the installation and operation of computers and other equipment comprising the System; and

(d) the starting date of installation of the System.

2) Licensed ROs shall be responsible for the cost of excise markings applicators, adjustments or adaptations of their equipment and premises necessary to install and integrate the new or modified System on each production line.

3) Where a licensed RO is required to carry out adjustments or provide information required by the Ministry for the installation of the new or modified System, such RO shall carry out the adjustments or provide the information at least seven calendar days before the date of the installation of the new or modified System.

## 23. የአስተዳደር ስርአቱ አካላት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 መሰረት የሚገጠመው ስርአት የሚከተሉትን የሚያጠቃልል ይሆናል፡-

## 23.COMPOSITION OF THE SYSTEM

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሀ) ለኤክሳይዝ ምልክቶች ማረጋገጫ እና እውቅና የሚሰጥ መሳሪያ፤

ለ) እያንዳንዱን መያዣ በተለየ የኤክሳይዝ ምልክት የሚለይ እና የሚያስተሳስር መሳሪያ፤

ሐ) የምርት ሂሳብ መመዝገቢያ መሳሪያ፤ እና

መ) ለታክስ ባለስልጣኑ መከታተያ ሆኖ የሚያገለግል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች ብዛት መቆጣጠር፤ መመዝገብና መረጃን ማስተላለፍ የሚያስችል መሳሪያ፤

The System to be installed in accordance with Article 15 of this Directive shall be composed of:

a) excise Markings authentication and validation equipment;
b) devices for identification and association of each package with an individual excise Markings;
c) production accounting equipment; and
d) devices for the control, registration, recording and transmission of data on quantities of excisable goods which have been Markings to the Tax Authority.

## 24. የአስተዳደር ስርአት ተከላ እና ማጣጣም

የአስተዳደሩ ስርአት አካል የሆኑ እና በአምራቹ የማምረቻ ቦታ ወይም በአስመጪው ማከማቻ ስፍራ እና በታክስ ባለስልጣኑ ዋና የመረጃ ማእከል እና የአደጋ መጠባበቂያ ማዕከል ስርዓት የሚገጠሙ መሳሪያዎች ተከላ፤ የማጣጣም ስራ እና የጥገና ወይም እድሳት ስራ የሚከናወነው የታክሱ ባለስልጣን በሚመድበው ስልጣን የተሰጠው ሰው ተቆጣጣሪነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በሚመረጠው ኩባንያ አማካኝነት ይሆናል፡፡

## 24. INSTALLATION AND SYSTEM INTEGRATION

The installation, integration, preventive and corrective maintenance procedures of all the equipment comprising the System at the manufacturers' or importers' premises, and the System at the main data center and disaster recovery center of the Tax Authority shall be done by a Company to be appointed in accordance with Article 10 of this Directive under the supervision of an authorized officer.

## 25. የማምረቻ መስመር በትክክል የሚሰራ መሆኑን ስለማረጋገጥ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የመሳሪያዎች ተከላ በሚደረግበት ወቅት የማምረቻ መስመሮች በትክክል የሚሰሩ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 25. ENSURING PROPER FUNCTIONING OF THE PRODUCTION LINE

During the installation of the System, the manufacturer or importer of excisable goods shall ensure that the production lines are in proper operating condition.

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

**26. አገልግሎት መስጠት ያቋረጡ የማምረቻ መስመሮችን ስለማስታወቅ**

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ አገልግሎት መሰጠት ያቋረጡ የማምረቻ መስመሮችን አገልግሎት መስጠት ካቋረጡበት ጊዜ አንስቶ በ24 ሰአት ውስጥ ይህንኑ ለታክሱ ባልስልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡ የታክሱ ባልስጣንም እነዚህን መስመሮች በማሸግ መስመሮቹ የታሸጉ ሰለመሆኑ በአስተዳደር ስርአቱ ላይ ይመዘግባል፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የታክሱን ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ የታሸጉትን የማምረቻ መስመሮች በመጠቀም ማምረት አይችልም፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም " አገልግሎት ያቋረጠ የማምረጫ መስመር" ማለት በቴክኒክ ችገር፤ በጥሬእቃ እጥረት፤ በገበያ መቀዝቀዝ ወይም በተመሳስይ ምክንያት ከ24 ሰአት በላይ ለሆነ ጊዜ የማይሰራ የማምረቻ መስመር ነው።

**27. የመሳሪያዎች ደህንነት**

1) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ በስራ ቦታው ለተገጠሙ መሳሪያዎች እና ለአስተዳደር ስርአቱ እንክብካቤ የማድረግ እና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የአስተዳደር ስርአቱ የማይሰራ በሚሆንበት ወይም የደህንነት መጠበቂያ ማሸጊያዎች የመነካካት አደጋ ባጋጠማቸው ጊዜ ይህንኑ በ24 ሰአት ጌዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**28. የመሳሪያዎች እድሳት ወይም ጥገና**

**26. REPORTING INOPERATIVE PRODUCTION LINES**

1) The manufacturer or importer of excisable goods shall report to the Tax Authority any non-operational production lines within twenty-four hours of the production lines becoming non- operational and the Tax Authority shall secure the lines using a security seal and register the seal in the System.
2) Manufacturer's or importers of excisable goods shall not resume operations on non-operational production lines without the authorization of the Tax Authority.
3) For the purpose of this Article " Non-operational Production Line" means a line which is not functioning for over 24 hours due to technical failures, shortage of raw materials, market slow down or any other similar reason.

**27. SECURITY OF EQUIPMENT**

1) A manufacturer or importer of excisable goods shall be responsible for conservation and security of the System installed in their premises.
2) Manufacturer or importer of excisable goods shall report any operating failure or tamper of the security seals within twenty-four hours.

**28. PREVENTIVE AND CORRECTIVE MAINTENANCE OF THE SYSTEM**

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

1) ኩባንያው የታክሱ ባለስልጣን በሚመድበው ስልጣን በተሰጠው ሰው ተቆጣጣሪነት ስር ሆኖ በአስተዳደር ስርአቱ ላይ እድሳት ወይም ጥገና ማድረግ አለበት።
2) ኩባንያው በአስተዳደር ስርአቱ ላይ እድሳት ወይም ጥገና የሚያከናውኑ ባለሙያዎችን የስም ዝርዝር እና ለስራው ያላቸውን አግባብነት ለታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ ማስታወቅ አለበት፡፡

1) The preventive or corrective maintenance of the System shall be performed by the Company under supervision of an authorized officer,
2) The Company shall provide the Tax Authority a list of technicians authorized to carry out the installation or maintenance of the System and their competence to do the job.

## 29. አዳዲስ የምርት አይነቶችን አስቀድሞ ስለማስታወቅ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች አምራች ወይም አስመጪ፡-

ሀ) ለውጭ ገበያ ወይም ለቀረጥ ነጻ መደብሮች የሚቀርቡትን ጨምሮ የሚያመርታቸው ወይም ወደአገር የሚያስገባቸውን እቃዎች መያዣዎች እና በእነዚህ መያዣዎች ላይ የሚደረገውን መግለጫ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፤
ለ) አዳዲስ ምርቶችን ማምረት ከመጀመሩ ወይም በነባር ምርቶቹ ላይ የሚደረገውን መግለጫ ወይም ማሸጊያ ከመለወጡ 60 ቀን በፊት ይህንኑ ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፤
ሐ) ለሚከተሉት ምክንያቶች የአስተዳደር ስርአቱን ከመዘርጋቱ ወይም ከማስወገዱ በፊት ባሉት 60 ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ የማቅረብ፤
(i) ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ የማምረቻ መስመሮችን ስራ ከማስቀጠሉ፤
(ii) የማምረቻ መስመሮችን ስራ ከማቋረጡ፤
(iii) በማምረቻ መስመሮች ላይ ጥገና ከማድረጉ ወይም የማምረቻ መስመሮችን ተግባር ከመለወጡ በፊት፤
(iv) አዲስ የማምረቻ መስመር ከመዘርጋቱ በፊት፤ ወይም
(v) አዲስ የማምረቻ መሳሪያ ከመግዛቱ ወይም የነበረውን የማምረቻ መሳሪያ ከመሸጡ በፊት፡፡

## 29.ADVANCE REPORTS OF NEW BRANDS

A manufacturer or importer of excisable goods shall:

a) declare to the Tax Authority the packages and labels of brands manufactured or imported including those for export and duty free shops;
b) declare to the Tax Authority at least sixty days before the start of the production of new brands of goods or any change in the graphic art of existing brands of goods and the corresponding packages and labels;
c) Submitting an application to the tax authority 60 days before establishing or removing the management system for the following reasons:
   i) before installation or removal, for the installation or removal of the System, as the case may be, if the manufacturer or importer reactivates inoperative production lines;
   ii) before deactivating production lines;

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 30. የኤክሳይዝ ምልክትን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ

1) ማናቸውም አምራች፤ አስመጪ፤ አከፋፋይ፤ቸርቻሪ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ማናቸውም ሌላ ሰው እቃዎቹን ከመረከቡ በፊት በእቃዎቹ ላይ የተደርገው የኤክሳይዝ ምልክት ትክክለኛ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

2) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያከፋፍል ወይም በችርቻሮ የሚሸጥ ሰው፡

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሚያመርት ሰው የተሰጠውን የማስረከቢያ ሰነዶችን፤ ደረሰኞችን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን ይዞ ማቆየት፤ እና

ለ) በስራ ቦታው የኤክሳይዝ ምልክትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ ብርሃን እንዲኖር የማድረግ፤
ግዴታ አለበት፡፡

## 31. የኤክሳይዝ ምልክትን አቅርቦት ስለመከልከል

የታክሱ ባልስልጣን የሚከተሉትን ፈጽሞ የተገኘ ሰው የኤክሳይዝ ምልክት እንዳይሰጠው ሊከለክል ይችላል፡፡

iii) before carrying out maintenance works on or reallocates production lines;

iv) before installing new production lines; or

v) before acquiring or selling industrial machinery or equipment.

# PART FOUR

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 30. OBLIGATION TO VERIFY EXCISE MARKINGS

1) A manufacturer, importer, distributor, retailer or any other person involved in the supply chain of excisable goods, shall verify and authenticate the Markings placed on excisable goods before admitting the goods in the manufacturer's, importer's, distributor's, retailer's or other person's premises.

2) A person engaged in the distribution or retail of excisable goods shall:

a) keep delivery notes, invoices or such other documents from the supplier of the excisable goods; and

b) provide in that person's premises sufficient light as may be necessary for the verification or authentication of excise Markings;

## 31. REFUSAL TO ISSUE EXCISE MARKINGS

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ሀ) አስቀድሞ የተሰጠውን የኤክሳይዝ ምልክት ሂሳብ ያላወራረደ፤

ለ) በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት የኤክሳይዝ ታክስን የማስታወቅ እና የመክፈል ግዴታውን ያልተወጣ፤

The Tax Authority may refuse to issue excise Markings to a person if that person:

a) has not fully accounted for excise Markings previously issued to him or her; and
b) failed to fully comply with the provisions of the Excise Tax Proclamation relating to filing of returns and payment of excise tax.

## 32. የኤክሳይዝ ምልክትን፣ መሳሪያዎችን እና እቃዎችን ስለመያዝ

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ በጉምሩክ አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ምልክቶችን፣ መሳሪያዎችን እና እቃዎችን ለመያዝ ይችላል፤

ሀ) የኤክሳይዝ ምልክትን በሚመለከት፤

(i) አስመስሎ የተሰራ ሆኖ ሲገኝ፤
(ii) ለታክሱ ባለስልጣን መመለስ ያለበት ሆኖ ሳለ፤ ያልተመለሰ ሆኖ ሲገኝ፤
(iii) ከተፈቀደለት ሰው ወጪ በሌላ ሰው ተይዞ ሲገኝ፤

ለ) በአዋጁ የተደነገገውን ለማያሟላ እቃ ማከማቻ፤ መሸሸጊያ ወይም ማጓጓዣ ውሎ የተገኘን ተሽከርካሪ፤

ሐ) የኤክሳይዝ ምልክትን አስመስሎ ለመስራት የሚውል መሳሪያ፤

መ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እቃዎች፤

(i) አስመስሎ የተሰራ የኤክሳይዝ ምልክት ተለጥፎባቸው የተገኘ እንደሆነ፤
(ii) በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጪ ተገቢ ባልሆነ አኳኋን የኤክሳይዝ ምልክት ተለጥፎባቸው የተገኘ እንደሆነ፤

## 32. SEIZURE OF EXCISE MARKINGS, EQUIPMENT AND GOODS

The Tax Authority shall, as provided in the Excise Tax Proclamation, the Customs Proclamation and Tax Administration Proclamation, seize excise Markings, equipment, vehicles or goods where:

a) with regard to excise Markings;
   (i) excise Markings have been counterfeited;
   (ii) which were subject to be returned to the Tax Authority, were not returned; or
   (iii) have been found in the possession of persons other than those to whom they were supplied;

b) the vehicle is used in the storage, concealment or transportation of excisable goods that have not met the requirements of these regulations;

c) the equipment or plant is used in the manufacture of counterfeit excise Markings; or

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

(iii) በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት የኤክሳይዝ ምልክት ሳይለጠፍባቸው የተገኘ እንደሆነ፤

d) with regard to the excisable goods-

(i) bear counterfeited excise Markings;

(ii) bear excise Markings affixed in a manner not consistent with this Directive; or

(iii) do not bear excise Markings as required in accordance with this Directive .

**33. አስመስለው የተሰሩ የኤክሳይዝ ምልክቶችንን ወይም የተያዙ እቃዎችን ስለማስወገድ**

የታክሱ ባለስልጣን አስመስለው የተሰሩ የክሳይዝ ምልክቶችን እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30 መሰረት የተያዙ ሌሎች እቃዎችን በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ለማስወገድ ይችላል፡፡

**33. DISPOSAL OF FORFEITED EXCISE MARKINGS, AND SEIZED GOODS**

Any excisable goods, Markings, motor vehicle and equipment which are seized under this Directive shall be disposed of by the Tax Authority in the manner prescribed under the Customs Proclamation.

**34. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ማናቸውም አስመጪ፣ አምራች፣ አከፋፋይ፣ቸርቻሪ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው እቃዎች አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ማናቸውም ሌላ ሰው በእጁ የሚገኙትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እና የኤክሳይዝ ምልክት ያልተደረገባቸውን ዕቃዎች የገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ምልክቶችን ለማግኘት የሚያስችል መመልከቻ መቀበሉን ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር ከ120 ቀናት በኋላ የኤክሳይዝ ምልክት ሳይለጠፍባቸው ወይም ምልክት ሳይደረገባቸው ለገበያ ማዋል አይችልም፡፡

**34. TRANSITORY PROVISION**

A manufacturer, importer, distributor, retailer or any other person involved in the supply chain of excisable goods, shall not transact with excisable goods in his hands on which excise Markings is not affixed or not marked after 120 days from the date the Tax Authority issues a notice through an official gazette in which it announces that it has started receiving applications for Excise Markings.

**35. ስለመሻር**

የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ስርዓትን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1004/2016 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

**35. Repeal**

The Excise Stamp Management Directive No.1004/2024 is hereby repealed.

**36. የሚጸናበት ቀን**

**36. EFFECTIVE DATE**

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ግንቦት 18 ቀን 2017 አ.ም

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

This Directive shall come into force on the date of its publication on the Ministry of Finance's official website following its registration with the Ministry of Justice.

Done at Addis Ababa on this 26th May of 2025

Ahmed Shide

Minister of Finance

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 23rd of June 2025.